www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለዉ የቢኒሻንጉል - ጉሙዝ

# ክልል ህገ መንግሥት

ህዳር 1995
አሶሳ

www.abyssinialaw.com

አዋጅ ቁጥር ______/1995

## የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ህገ- መንግሥት

በክልሉ ነዋሪ ህዝብ በሰፊውና በዝርዝር ተመክሮበት እስከ አሁን በሥራ ላይ የቆየውን ህገ መንግሥት አሁን በተጨባጭ እየታየ ባለው አጠቃላይ ሁኔታ የክልሉ መንግሥት አካላትን የሥልጣን ክፍፍልና ተጠያቂነት በግልፅ በሚያሳይ መልኩ ማሻሻሉ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በሥራ ላይ ባለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ህገ መንግሥት አንቀጽ 99 መሠረት ይህ የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም የክልሉ ህገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ህገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር______ 1995 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም ህገ መንግሥት ስለመፅደቁ

በአዋጅ ቁጥር 2/1988 የፀደቀው የክልሉ ህገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ በስፋት ከታየ በኋላ በ1995 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ህገ መንግሥት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

3. ስለነባር ህጎች ተፈፃሚነት

በሥራ ላይ ያለ ማንኛውም ነባር ህግ ከተሻሻለው ህገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ከዛሬ ______ ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አሶሳ

______ቀን 1995 ዓ.ም

ያረጋል አይሸሽም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት

# የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ህገ- መንግሥት

www.abyssinialaw.com

## መግቢያ

እኛ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ ተመስርተን በአቋቋምነው ክልላችን የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ቋንቋችንን፣ባህላችንና እድገታችንን ይበልጥ ለማጠናከር፣ማንነታችን ተከብሮ በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዲሞክራሲና ሠላም በዘላቂነት ለማረጋገጥ፣

እኛ የክልሉ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳችን መልክዓ ምድራዊ አሠፋፈር ያለን፣ለረጅም ዘመን በተለያዩ መልኮችና ደረጃዎች ተሳስረን የቆየን በመሆናችን በጋራ ያፈራናቸው እሴቶች ላይ በመመስረትና በማጎልበት ወደ ተሻለ የእድገት ጎዳና እንድናመራ ፅኑ እምነት ያለን በመሆኑ፣

በሥራ ላይ የነበረው ሕገ መንግሥታችን ግልፅ አሠራርና የሥልጣን ክፍፍልን የማያሳይ፣ለመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለው የመንግሥት አካላት አደረጃጀት የማያመለክት፣የሚፈለገውን ፈጣን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ማምጣት የማያስችል ስለሆነ እንደገና ተሻሽሎ መውጣት የሚገባው መሆኑን በመገንዘብ፣

እኛ የበርታ፣ የጉሙዝ፣ የሽናሻ፣ የማኦና የኮሞ ብሄረሰቦች እና ሌሎች በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ለዘላቂ ሠላምና ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክን ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገና የክልላችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘበ ሕገ መንግሥት ሲኖረን መሆኑን በውል በመረዳት ፣

እስከ አሁን በሥራ ላይ የነበረው የ1987 ዓ.ም ህገ መንግሥታችንን አሁን በተጨባጭ እየታየ ባለው ሀገራዊ እና ክልላዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ግልፅ አሠራርን የሚከተል፣ ለመረጠው ህዝብ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለው መንግሥታዊ አደረጃጀትን በሚያመላክት መልኩ አግባብ ያለው ጥልቅ እይታ ተደርጎበት ተሻሽሎ መውጣት ያለበት መሆኑን በማመን፣

እነሆ ዛሬ ህዳር 23 ቀን 1995 ዓ.ም በአሶሳ ከተማ ባካሄድነው የክልሉ ምክር ቤት 1ኛ አስቸኳይ ጉባኤ የቀረበውን የተሻሻለ የክልሉ ህገ መንግሥት መክረንና በዝርዝር ተወያይተን አፅድቀነዋል።

## ምዕራፍ አንድ

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 1

የክልሉ መንግሥት ስያሜ

ይህ ህገ መንግሥት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የሚቋቋመው መንግሥት "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት" በሚል ስም ይጠራል።

## አንቀጽ 2

የክልሉ ባለቤት ብሄረሰቦች

በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች የሚታወቁ ቢሆንም የክልሉ ባለቤት ብሄር ፣ብሄረሰቦች በርታ፣ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ ናቸው።

## አንቀጽ 3

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ክልል ወሰን

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ከአማራ ክልል፣በምሥራቅ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ከጋምቤላ ሕዝቦች ክልል እና በምዕራብ ከሱዳን ጋር ይዋሰናል።

## አንቀጽ 4

ሰንደቅ አላማና አርማ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የራሱ ሰንደቅ ዓላማና አርማ ይኖረዋል።

1. ሰንደቅ ዓላማው ቀይ፣ጥቁር፣ቢጫ፣አረንጓዴ እና ዙሪያው ነጭ ፍሬም ያለው ይሆናል።
2. የክልሉ ዓርማ ዙሪያው በቀርከሃ የተከበበ ሆኖ በመሀሉ ወርቅ የያዘ ገበታ እና የማሽን ጥርስ ያለው ይሆናል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል ።

## አንቀጽ 5

የክልሉ ህዝብ መዝሙር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የራሱ የሆነ ብሄራዊ መዝሙር ይኖረዋል። የክልሉ መዝሙር የህገ መንግሥቱን ዓላማዎችና የክልሉን ህዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የወደፊት የጋራ እድላቸውን የሚያንፀባርቅ ሆኖ በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 6

ቋንቋ

1. የክልሉ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው።
2. የክልሉ ቋንቋዎች ሁሉ በዚህ ህገ መንግሥት እኩል እውቅና ይኖራቸዋል።
3. በክልሉ የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦች በራሳቸውና በፈለጉት ቋንቋ የመማር መብት አላቸው።

## አንቀጽ 7

ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕሰ ከተማ አሶሳ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 8

### የፆታ አገላለፅ

በዚህ ህገ መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴቷንም ፆታ ያካትታል።

# ምዕራፍ ሁለት

## የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

## አንቀጽ 9

### የህዝቡ ወሳኝነት

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝብ የክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤት ነው።
2. የህዝቡ የበላይነት የሚገለፀው በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በቀጥታ በሚያደርገው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

## አንቀጽ 10

### የህገ መንግሥቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. ይህ ህገ መንግሥት የክልሉ የበላይ ህግ ነው። ማንኛውም ህግ፣ልማዳዊ አሠራር፣እንዲሁም የማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግሥት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅትና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ህገ መንግሥቱን የማስከበርና ለህገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።
3. በዚህ ህገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 11

www.abyssinialaw.com

### ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።
2. የግለሰቦችና የህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀጽ 12

### የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

## አንቀጽ 13

### የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ህዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ አምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. ማንኛውም ኃላፊና የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

# ምዕራፍ ሶስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

## አንቀጽ 14

### ተፈፃሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የህግ አውጪ፣ የህግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግጋት፣ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

# ክፍል አንድ

## ሰብአዊ መብቶች

## አንቀጽ 15

### የህይወት፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

## አንቀጽ 16
### በህይወት የመኖር መብት

www.abyssinialaw.com

ማንኛውም ሰው በህይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በህግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ህይወቱን አያጣም።

## አንቀጽ 17
### የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው የአካል ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 18
### የነፃነት መብት

1. በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነፃነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

## አንቀጽ 19
### [illegible]

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብአዊ በሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። [illegible] ተግባር የተከለከለ ነው።

3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት" የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፡

[illegible]

በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውንም ሥራ፣

ለ/ ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ህሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ሐ/ የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣ www.abyssinialaw.com

መ/ በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀመውን ማንኛውንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ሥራ፣

## አንቀጽ 20
### የተያዘ ሰው መብት

1. ወንጀል ፈፅሟል በመባል የተያዘ ሰው የቀረበበት ክስና ምክንያት በዝርዝርና ወዲያውኑ በሚገባው ቋንቋ እንደነገረው መብት አለው።

2. የተያዘ ሰው ላለመናገር መብት አለው። የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠው መብት አለው።

3. የተያዘ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው። ሆኖም ይህ የጊዜ ገደብ ሰውዬው ከተያዘበት ቦታ ወደ አቅራቢያው ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ማምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበም በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሠር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለፅለት መብት አለው።

4. የያዘው አካል /ፖሊስ/ ወይም የህግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ ግለሰቡ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የህግ አስከባሪ ባለሥልጣናት ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።

5. የተያዘ ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

6. የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው። ሆኖም በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

## አንቀጽ 21
www.abyssinialaw.com
### የተከሰሰ ሰው መብት

1. በወንጀል የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለህዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው። የተከራካሪውን የግል ሕይወት፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረውና ክሱን በፅሁፍ የማግኘት መብት አለው።
3. በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል አንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለው።
4. የተከሰስ ሰው የቀረበበትን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት የቀረበበትንም ምስክር የመጠየቅ ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበው እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለው።
5. በመረጠው የህግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣቱ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለው።
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው።
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 22
### በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው መብት

1. በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው ሰብአዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለው።
2. ከትዳር ጓደኛው፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቹና ከሀኪሞቹ ጋር የመገናኘትና እንዲጎበኙት ዕድል የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 23
### የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በህግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ ህግ ለተከሣሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 24
### በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀጽ 25
### የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው ሰብአዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሣደግ መብት አለው።

## አንቀጽ 26
### የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሄር፣ በብሄረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት ፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 27
### የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱና ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለን ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያጠቃልላል።
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚፅፋቸውና የሚፃፃፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።
3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሄራዊ ደህንነትን ፣ የህዝብን ሠላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ህጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

## አንቀጽ 28
### የሃይማኖት፣ የህሊናና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻው ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል።

www.abyssinialaw.com

2. በዚህ ህገ መንግሥት አንቀጽ 112 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችላቸውን የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማትን ለማቋቋም ይችላሉ።

3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።

4. ወላጆችና ህጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሣደግ መብት አላቸው።

5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለው የህዝብን ደህንነት፣ ሠላም፣ ጤና፣ ትምህርት፣ የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶች ፣ ነፃነቶችና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ህጎች ይሆናል።

## አንቀጽ 29
### በሰብዕና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች "በሰው ልጅ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች" ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅነት ሰውን የመሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይረጋ አይታገድም። በህግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም።

## ክፍል ሁለት
### ዲሞክራሲያዊ መብቶች

### አንቀጽ 30
#### የአመለካከት ፣ ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት መያዝ ይችላል።

2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በፅሁፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሠራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሠራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።

3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፣

   ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

   ለ/ የህዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን፣

4. ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶችን የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የህግ ጥበቃ ይደረግለታል።

www.abyssinialaw.com

5. በክልሉ መንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመሥርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።

7. ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ህጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በህግ [illegible]

## አንቀጽ 31
### የመሰብሰብ፣ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሠላም የመሰብሰብ፣ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ ነፃነትና [illegible] ሠልፍ ሠላምን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብነት ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

## አንቀጽ 32
### [illegible]

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሠረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 33
### የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ [illegible] የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት፣ ሀገሩ የመምረጥ፣ ሀብትና ንብረት የማፍራት፣ የመያዝ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

## አንቀጽ 34

www.abyssinialaw.com

**በሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራዎች የመሥራት መብት**

1. የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቁ የሌሎች ክልሎች ተወላጆች የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ክልል ውስጥ እንደማንኛውም የዚህ ክልል ተወላጅ የመኖር፣ በማንኛውም የክልሉ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራ ውስጥ ተቀጥረው ወይም ተመድበው የመሥራት መብት አላቸው።

2. ማንኛውም ሰው በክልሉ የመኖር፣ከሥፍራ ሥፍራ በነፃ የመዘዋወር፣ሀብትና ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብት አለው።

## አንቀጽ 35

**የጋብቻ የግልና የቤተሰብ መብቶች**

1. በሕግ በተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሄር፣ ብሄረሰብ፣ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈጻፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺ ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ የህግ ድንጋጌዎች ይወጣሉ።

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሠረታል፣

3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ስለሆነም ከህብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።

4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖት፣ በባህልና በህግ ሥርዓቶች ላይ ተመሥርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።

5. ይህ ሕገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 36

**የሴቶች መብት**

1. ሴቶች ይህ ሕገ - መንግሥት በአረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይኸው የታሪክ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። በዚህ ረገድ የሚወሰዱት እርምጃዎች አላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

4. ሴቶች ከጎጂ ልማድ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑና በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።

www.abyssinialaw.com

5. ሴቶች የቅጥር፣የሥራ እድገት፣የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።

6. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሠሩ ሴቶች፣

ሀ/ የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፣ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት ፣የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል።

ለ/ የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል።

7. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።

8. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።

9. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች፣ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

## አንቀጽ 37
### የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት።

   ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

   ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

   ሐ/ ወላጆቹን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

   መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

   ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በህፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፣

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በማቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙና በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም በግል አሳዳጊ ማውታን ተቋሞች የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።

www.abyssinialaw.com

4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው።

5. መንግሥት ለአሳዳጊዎቻቸው ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠርቱ ያበረታታል።

## አንቀጽ 38

### ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ ፣

   ሀ/ ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

   ለ/ ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሣሣይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 39

### የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባለቤት ብሄር ብሄረሰቦች መብቶች

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብሄር ብሄረሰቦች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህም መሠረት የክልሉ ብሄር ብሄረሰቦች ፣

1. የራሳቸውን ብሄራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ እንዲሁም እያንዳንዱ ብሄረሰብ በቋንቋው የመጠቀም፣ ቋንቋውን የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው።

2. በራሳቸው መልክዓ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመጨረስ፣ራስን በራስ የማስተዳደር እንዲሁም በፌዴራሉ መንግሥት ውስጥ በነፃነት፣እድልዎ በሌለበት ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ የማድረግ መብት አላቸው።

3. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብሄር ብሄረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል መንግሥቱ አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት አለው።

4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተጠቀሱት መብቶች ታግደ ተረገጡ ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና እነኝህንም በአንድነት ሥር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ ተግባራዊ ያደርጋል።

5. የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በሥራ ላይ የሚውለው፣

ሀ/ የመገንጠል ጥያቄ በብሄር ፣በብሄረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ ፣

ለ/ የፌዴራሉ መንግሥት የብሄር ፣የብሄረሰቡ ወይንም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሄር ፣ብሄረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣

ሐ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔው በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ፣

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠው ብሄር ፣ብሄረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ ፣

ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. የክልሉ ብሄር ፣ ብሄረሰቦች በማንኛውም ጊዜ የራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው ። አፈፃፀሙ በፌዴራል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ- መ) ይሆናል።

7. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ " ብሄር፣ ብሄረሰብ ፣ ሕዝብ " ማለት ቀጥሎ የተገለፁትን ባህሪያት የሚያሳይ ማህበረሰብ ነው። ሰፊ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሣይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑና የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው።

## አንቀጽ 40
### የንብረት መብት

1. በክልሉ ውስጥና ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል። ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎች ዜጎችን መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ " የግል ንብረት " ማለት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ህጋዊ ሰውነት በህግ የተሰጣቸው አገር አቀፍ ወይም ክልላዊ ማህበራት ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በህግ በተለይ በጋራ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች፣ በጉልበታቸው፣ በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው የአፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ሕዝብ የጋራ ንብረት ነው።

www.abyssinialaw.com

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ ነው። አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል።

5. በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮችና ከፊል አርሶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። አፈፃፀሙ በህግ ይወሰናል።

6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

7. በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህም መብት የመሸጥ ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ደግሞ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብቶችን ያካትታል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 41
### የኢኮኖሚ፣የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. የክልሉ ነዋሪ የሆነ ወይም በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት አለው።

2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።

4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

5. የክልሉ መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

6. የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ አድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

8. አርሶ አደሮችና ከፊል አርሶ አደሮች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሄራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። የክልሉ መንግሥት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።

www.abyssinialaw.com

9. የክልሉ መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 42
### የሠራተኞች መብት

1. የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች:-

ሀ/ የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብቶችን ያካትታል።

ለ/ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታ ለማሰማት መብት አላቸው።

ሐ/ ከፍ ብሎ በፊደል ሀ እና ለ መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በህግ ይወሰናሉ።

መ/ ሴት ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት፣ ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀናት፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 43
### የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሄራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል።

## አንቀጽ 44
### የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።

2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሄዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

# ምዕራፍ አራት
## የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል

## አንቀጽ 45
### የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. ክልሉ በክልል ፣በብሄረሰብ ምክር ቤትና በአስተዳደራዊ እርከኖች የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖችን በሕግ ሊያዋቅር፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን በህግ ሊወስን ይችላል።

2. በክልሉ ውስጥ የሚቋቋሙት የመስተዳደር እርከኖች በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ መሠረት ያደረጉ ናቸው ።
3. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ህዝቦች ውክልና በልዩ ሁኔታ የሚታይ ይሆናል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ልማታቸውን የሚያፋጥን የራሣቸው አስተዳደር ይኖራቸዋል ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 46
### የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ሕግ አውጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለወከለው ሕዝብ ነው።

2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።

3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 47
## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ውስጥ በውል ተለይተው ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያለ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግሥቱ :-
   2.1 የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ያስፈጽማል፣
   2.2 የክልሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል ያስፈጽማል፣
   2.3 የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፣

   2.4 ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማው ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትንና ይህንን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፣

   2.5 የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህንኑ በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

   2.6 የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣
   2.7 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሕግ መሠረት ምህረት ያደርጋል፣

   2.8 ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ የክልሉን በጀት ያወጣል፣ ያስፈፅማል ፣

   2.9 በክልል መስተዳድሩና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ይሰበስባል፣
   2.10 የመሬት መጠቀሚያ ክፍያን ይወስናል ፣ ይሰበስባል፣
   2.11 የአርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣
   2.12 በክልሉ ውስጥ በግል ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፣
   2.13 በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብርና የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣
   2.14 ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር:-
      ሀ/ በጋራ ከሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን በሕጉ መሠረት ይካፈላል፣

www.abyssinialaw.com

ለ/ ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክሶችን በሕጉ መሠረት ይካፈላል፣

ሐ/ ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕጉ መሠረት ይካፈላል፣

2.15 በክልል መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል።

2.16 ከደን የሚገኘውን የሮያሊቲ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል።

2.17 በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊ/ሄ አዋጅ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ አምስት
## ስለክልሉ ምክር ቤት

## አንቀጽ 48
### ስለክልሉ ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ ፣ ቀጥተኛ ፣ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በምስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትን መሠረት ያደረገ ይሆናል። የማኦና የኮሞ ብሄረሰቦች ውክልና በልዩ ሁኔታ ይታያል ። በቅላላ የክልል ምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአንድ መቶ አይበልጥም። የተለየ ውክልና እንደሚያስፈልጋቸው የታመነባቸው ሕዝቦች በምርጫ ምክር ቤቱ ውስጥ ይወከላሉ። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3. የምክር ቤቱ አባላት የመላው የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም:-

   ሀ/ ለሕገ መንግሥቱ

   ለ/ለመረጣቸው ሕዝብና

   ሐ/ለራሳቸው ሕሊና ብቻ ይሆናል።

4. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም።

5. ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም።

6. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል።

7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ድንጋጌ እንደአግባብነቱ በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 49
### የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ሕግ አውጭ አካል ነው።

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

3.1 በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የፌዴራሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን የማይጻረሩ ልዩ ልዩ ሕጎችን ያወጣል።

www.abyssinialaw.com

3.2 የሕዝቡን ብዛት፣ የክልሉን ስፋትና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ ውስጥ ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደራዊ አካባቢዎችን በሕግ ያቋቁማል፣

3.3 የፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጎራባች ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ያፀድቃል፣

3.4 የራሱን አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመርጣል፣ ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይሰይማል፣

3.5 ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን በምርጫ ይሰይማል፣ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል፣

3.6 በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል፣

3.7 የክልሉን ጠቅላይ፣ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን ያቋቁማል፣ዳኞችን ይሾማል።

38 የኦዲትና ሌሎች የቁጥጥር አካላቱን ያቋቁማል።

3.9 የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሉን ያቋቁማል፣

3.10 የክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ያፀድቃል፣

3.11 የክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጎችን ያወጣል፣ የክልሉን በጀት ለብሄረሰብ ምክር ቤቶች ለአስተዳደራዊ እርከኖችና ወረዳዎች በቀመር ይመድባል፣ መርምሮ ያፀድቃል፣

3.12 ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠንና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል፣

3.13 ለክልሉ መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል፣

3.14 የክልል መስተዳድሩን የሠራተኛ አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣

3.15 በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 2 (2.17) ሥር ለክልሉ መንግሥት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል፣

www.abyssinialaw.com

3.16 የሀገሪቱንና የክልሉን ሕግጋተ መንግሥታት አዋጆችና ሌሎች ሕጎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ደንቦችን ያወጣል፣

3.17 የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈፃሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀጽ 50
### የፖለቲካ ሥልጣን

1. በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ያደራጃል፣ ወይም ያደራጃሉ፣ ይመራል ወይም ይመራሉ፣

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደየአግባብነቱ ለብሄረሰብ ምክር ቤት፣ ለወረዳ እና ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 51
### ስለክልሉ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 52
### ስለምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(3.4) መሠረት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
2. አፈ ጉባኤው የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 53
### የአፈ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ይመራል፣
2. ምክር ቤቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፣
3. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣
4. ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ እንዲወሰድ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፣
5. የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያስተባብራል።

## አንቀጽ 54

የምክትል አፈ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር
www.abyssinialaw.com

ምክትል አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤውና ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ :-

1. በአፈ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. አፈ ጉባኤው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

## አንቀጽ 55
### የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ የስብሰባው ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል።
3. የክልሉ ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት ለአምስት ዓመታት ነው። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።
5. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፣ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈፃሚ አካል ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

## አንቀጽ 56
### የምክር ቤቱ ውሣኔዎችና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች

1. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ተገልጾ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሣኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይሆናል።
2. ምክር ቤቱ ውስጣዊ አሠራሩንና የሕግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ ስድስት

## ስለ የሕግ አስፈፃሚ አካል

### አንቀጽ 57
### የአስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።
4. " መስተዳድር " ማለት የክልሉ መንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል ነው።

### አንቀጽ 58
### የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎችና በሕግ በሚወስነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነው።
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው።
4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል።

### አንቀጽ 59
### የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ምክር ቤትና በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ሕጎችና የተላለፉ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል፣
2. የክልል መስተዳድሩን አስፈፃሚ አካላትና የሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣
3. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ3 (3.2) ድንጋጌዎች ሥር ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚቀርቡ የሽግሽግ ጥያቄዎችን አጥርቶ ይወስናል፣
4. የክልሉን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

5. የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ [illegible] www.abyssinialaw.com ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣የተወሰነውንም ያስፈፅማል፣

6. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣በሕግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል፣

7. የክልሉ ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፣

8. በዚህ ህገ መንግሥት አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3(ሸ) መሠረት የሚቀርቡለትን ኃላፊዎች ያሾማል ።

9. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (3.15) ሥር ለክልሉ ምክር ቤት አስቀድሞ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ችግርና ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ በክልሉ ውስጥ በሚደርስበት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፣

10.የክልሉ ቅርሳቅርስና የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ያረጋግጣል።

11. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 60
### የርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል፣

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የሥራ ዘመን የክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

## አንቀጽ 61
### የርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልል መስተዳድር ሥራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የክልሉ ፕሬዚዳንት ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፣
   ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ያስተባብራል፣ይወክላል፣
   ለ/ የክልሉ መንግሥት ሕግ አውጭና ሕግ አስፈፃሚ አካላት በየበኩላቸው መክረው ያፀደቋቸውን አዋጆችና ደንቦች በክልሉ ልሳነ ህግ ጋዜጣ ይታወጁ ዘንድ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ፈርሞ ይልካል፣ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይውላል፣
   ሐ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል፣
   መ/ በሕግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል፣
   ሠ/ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣የክልሉን ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር መርጦ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስሾማል፣

www.abyssinialaw.com

ረ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን ጨምሮ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሚሆኑ የመስሪያ ቤት ኃላፊችን ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል። ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ ምክር ቤት አባል መሆን አለበት።

ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥሮች ሠ እና ረ ሥር የሰፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ፣የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በመለስ ያሉትንና ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በጊዜያዊነት የሚመደቡት ከዳኞች መካከል ይሆናል፣

ሸ/ ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጭ የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች፣ ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችን መርጦ በመስተዳድሩ ምክር ቤት ያሾማል፣

ቀ/ የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ይቆጣጠራል፣

በ/ በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር አርከኖች ሥራ ይመራል፣ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፣

ተ/ የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፣

ቸ/ ለክልል ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

ኘ/ በክልል ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 62
### የምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ሹመቱ የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

   ሀ/ በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

   ለ/ ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

2. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 63
### የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በዚህ ሕገ መንግሥት የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ያስቻለው ዘንድ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።

2. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 64
ስለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

1. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊና አስተዳደራዊ የእለት ተእለት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች፣ኮሚሽኖችና ሌሎች ተቋማት እንደአስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ፣

2. የቢሮዎች፣የኮሚሽኖችና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ይሆናል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ ቢሮዎች፣ኮሚሽኖችና ሌሎች ተቋማት ተጠሪነት ከተቋቋሙበት አላማና ከሚያስፈጽሙት ተልዕኮ ጋር አግባብነት ላላቸው የክልሉ መንግሥት የበላይ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ይሆናል፣ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## ምዕራፍ ሰባት
ስለፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

## አንቀጽ 65
ስለነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል።
2. የዳኝነትን ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጪ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

## አንቀጽ 66
ስለ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካላት

በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሠራባቸው የነበሩ ሐይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ።

## አንቀጽ 67
የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው።
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ። ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የጡሮታ መውጫ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፣

www.abyssinialaw.com

ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲስፒሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈፅሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፣

ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፣

ሐ/ የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ የአብላጫ ድምፅ ሲደገፍና ሲፀድቅ።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የሰፈሩት ድንጋጌዎች አፈፃፀም ዝርዝር በሕግ ይወሰናል።

6. የማንኛውም ዳኛ የጡሮታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀጽ 68
## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣በከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል። የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣

ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን፣

ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣንና፣

ሐ/ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለው ክልላዊ ሥልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።

6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።

7. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚፈፅሙትን ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን የገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌዴራል መንግሥቱ ማካካሻ እንዲሰጣቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል።

## አንቀጽ 69
## ስለዳኞች አሿሿም

www.abyssinialaw.com

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት፣ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።

2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።

3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ። የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞችን ሹመት ለምክር ቤቱ ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳር ጉባኤ በዕጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና አስተያየቱን ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አስተያየቱን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልል ምክር ቤት ሹመቱን ያፀድቃል።

## አንቀጽ 70
### ስለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ጉባኤውን በሰብሳቢነት ይመራል።
3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር፣ስብጥር፣ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 71
### ሕገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን

1. በክልሉ ውስጥ የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሣ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ከአያንዳንዱ የክልል ባለቤት ብሄረሰብ አራት ሰው በጠቅላላው ሃያ አባላት የሚገኙበት በውክልና የሚሰየም የሕገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በዚህ ህገ መንግሥት ተቋቁሟል። አባላቱን የሚመርጡት የየብሄረሰብ ምክር ቤቶች ይሆናሉ።

2. ኮሚሲዮኑ የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርበለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ መክሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቋቋመው ኮሚሲዮን የአገልግሎት ዘመን የክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ሲሆን ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይሰበሰባል።

4. ኮሚሲዮኑ የራሱን ሰብሳቢና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል መርጦ ሥራውን የሚያከናውን ሲሆን ለሥራው የሚያስፈልገውን የጽሕፈት ቤት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከክልሉ ምክር ቤት ያገኛል።

## አንቀጽ 72
### የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል።

www.abyssinialaw.com

2. የክልሉ ህገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አሥራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሰብሳቢ፣

ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ/ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾሙና በሙያ ብቃታቸውም ሆነ በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች አባላት፣

መ/ በአፈ ጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየሙ ሶስት ተወካዮች አባላት፣

## አንቀጽ 73
### የአጣሪ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይህንን ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገው ከክልሉ የሚመነጩ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራት መሠረትም የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል።

2. አጣሪ ጉባኤው በክልሉ መንግሥት አካላት የሚወጡ ሕጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሲዮኑ ያቀርባል።

3. በፍርድ ቤቶች ዘንድ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ጉባኤው፣

ሀ/ የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል። ሆኖም ባጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለኮሚሲዮኑ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

ለ/ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለኮሚሲዮኑ ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል።

## ምዕራፍ ስምንት
### የብሄረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 74
### የብሄረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀት

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ከክልል ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው ።
2. እያንዳንዱ የብሄረሰብ አስተዳደር የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፣

ሀ/ የብሄረሰብ ምክር ቤት፣

ለ/ የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ፣

ሐ/ የብሄረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካል ፣

## አንቀጽ 75

www.abyssinialaw.com

## የብሄረሰብ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. እያንዳንዱ የብሄረሰብ ምክር ቤት ለክልል ምክር ቤት አባልነት የተመረጡትን ጨምሮ በውስጡ ከታቀፉት የወረዳ ምክር ቤቶች በልዩ ሁኔታ የሚመረጡ አባላት ያሉበት ሆኖ ይቋቋማል ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ለፌዴራል የህዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግሥት ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የብሄረሰብ ምክር ቤቶች የየብሄረሰባቸው የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልል ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

   ሀ/ የሚጠቀምበትን የሥራ ቋንቋ ይወስናል ፣

   ለ/ ብሄረሰቡ በቋንቋው ለመናገርና ለመጻፍ፣ ቋንቋውን ለማሳደግ፣ ለመጠበቅ፣ ለመግለጽ ፣ለማዳበርና ለማስፋፋት ፣ እንዲሁም ታሪኩን ለመንከባከብ ያለውን መብት ማስጠበቅ፣

   ሐ/ በዚህ ህገ መንግሥት ለክልል ምክር ቤት የተሰጠው የሕግ አውጭነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተደራጀበት አካባቢ ከክልል አቀፍ ሕግጋት ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በማይጻረር ሁኔታ የራሱን ዝርዝር የአፈጻፀም መመሪያዎች አውጥቶ ሥራ ላይ ያውላል።

   መ/ የክልሉ ምክር ቤት ያፀደቀውን እቅድና በጀት መሠረት በማድረግ የአካባቢውን ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል ።

   ሠ/ የብሄረሰብ ምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤንና ዋና አስተዳዳሪውን መርጦ ይሰይማል ።

   ረ/ በዋና አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን የብሄረሰብ አስተዳደሩን ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያፀድቃል ።

   ሰ/ በብሄረሰብ አስተዳደሩ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ላይ የበኩሉን አስተያየት ለክልሉ ምክር ቤት ይሰጣል።

   ሸ/ የብሄረሰብ አስተዳደሩን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የአስተዳደር ባለሥልጣናትን ለጥያቄ ይጠራል አሠራራቸውንም ይመረምራል ።

## አንቀጽ 76

## የብሄረሰብ ምክር ቤት አመራር

www.abyssinialaw.com

1. የብሄረሰብ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት ኖሮት ምክር ቤቱ ከአባላቱ መካከል በሚመርጠው የራሱ አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. የአፈ ጉባኤውንና ምክትል አፈ ጉባኤውን ዝርዝር ሥልጣንና ኃላፊነቶች አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ የተፃፉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

3. ምክር ቤቱ ለሥራው እንደአስፈላጊነቱ ራሱን በልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል።

## አንቀጽ 77

### የብሄረሰብ ምክር ቤት የሥራ ዘመንና የስብሰባ ጊዜ

1. የብሄረሰብ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል ። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል ።

2. የብሄረሰብ ምክር ቤት ቢያንስ በአመት ሦስት ጊዜ ይሰበሰባል ።

3. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል ። የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት አብላጫ ድምፅ ይተላለፋል ።

4. የብሄረሰብ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የብሄረሰብ አስተዳደሩ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤት አባላት መካከል አንድ ሶስተኛው የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 78

### የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚ አካል የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚመለከተው ብሄረሰብ አስተዳዳር ዋና አስተዳዳሪና ለብሄረሰቡ ምክር ቤት ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ለክልሉ አስተዳደር ምክር ቤትና ለርዕሰ መስተዳድሩ ተጨማሪ ተጠሪነት ይኖርበታል።

3. የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የብሄረሰብ አስተዳደሩ ዋና አስተዳዳሪ ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ የአስፈፃሚ መምሪያ ኃላፊዎች የሚካተቱበት አካል ሆኖ ይቋቋማል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 79

### የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ/ የብሄረሰብ ምክር ቤቱ በክልል ምክር ቤትና በፌዴራል መንግሥት አካላት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በአስተዳደሩ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፣
   ለ/ የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት የሆኑ መምሪያዎችንና ሌሎች አስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ በበላይነት ይመራል፣
   ሐ/ የአስተዳደሩን ዓመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ለብሄረሰብ ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ሲፈቀድም በተግባር እንዲውል ያደርጋል፣
   መ/የአስተዳደሩን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊስዎችና ስትራቴጂዎች በዝርዝር ይነድፋል። በብሄረሰብ ምክር ቤቱ ያፀድቃል፣ የተወሰነውንም ያስፈፅማል፣
   ሠ/ በብሄረሰብ አስተዳደር ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የሕዝቡ ሠላምና ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣል፣
   ረ/ በብሄረሰብ ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
2. የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔና ለሚፈፅሙት ተግባራት የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 80

### የብሄረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ በብሄረሰብ ምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከብሄረሰብ ምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል ።
2. በዚህ ህገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የዋና አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

## አንቀጽ 81

### የዋና አስተዳዳሪው ሥልጣንና ተግባር

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ የአስተዳደሩ ሥራ መሪ፣ የአስተዳደር ምክር ቤት ሰብሳቢና ተጠሪ ነው።
2. ዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለብሄረሰብ ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ነው።
3. ሌሎች የዋና አስተዳዳሪውን ሥልጣንና ተግባራት በሚመለከት በዚህ ሕገ መንግሥት የርዕሰ መስተዳድሩን ሥልጣንና ተግባራት አስመልክቶ የተዓፉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 82

### የብሄረሰብ አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ በዋና አስተዳዳሪው አቀራቢነት ሹመቱ በብሄረሰብ ምክር ቤት የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
   ሀ/ በዋናው አስተዳዳሪውና በብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቱ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ፣
   ለ/ ዋናው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣
2. ምክትል አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለዋናው አስተዳዳሪውና ለብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 83

### የዋና አስተዳዳሪው ጽህፈት ቤት

1. የብሄረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት የብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

### ስለወረዳ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 84

### አደረጃጀት

የወረዳ አስተዳድር የሚከተሉት አበይት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል።

1. በሥሩ ከተደራጁ ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮች ተዋጽኦ የሚቋቋም የወረዳ ምክር ቤት፣
2. ከዚሁ ምክር ቤት አባላት መካከል ተመርጦ በሚሰየም የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አማካይነት፣ የሚቋቋም የአስተዳደር ምክር ቤትና
3. በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የተቋቋመ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ይኖረዋል ።

## አንቀጽ 85

### የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት እቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግሥት አካላት በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች ፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ሥልጣን ይኖረዋል።

www.abyssinialaw.com

2. እያንዳንዱ ወረዳ እራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮቹ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተዳድር የበታች አካል ነው።

## አንቀጽ 86
## ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀጽ 87
## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግሥታዊ የሥልጣን አካል ነው። ተጠሪነቱ እንደአግባብነቱ ለብሄረሰብ ምክር ቤት ወይም ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

   ሀ/ የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ማህበራዊ አገልግሎቶች፣አስተዳደራዊ የሥራ እቅዶች፣ ፕሮግራሞችና በጀት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፣

   ለ/ በወረዳው ውስጥ መሠረታዊ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወኑን ይከታተላል፣

   ሐ/ ነዋሪው ሕዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

   መ/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አፈ ጉባኤውን፣ ምክትል አፈ ጉባኤውንና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል፣ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያፀድቃል።

   ሠ/ የራሱን ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣

   ረ/ ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርና ሌሎች ገቢዎች ወቅቱን ጠብቀው መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፣

   ሰ/ ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጪ ያለውንና የወረዳውን የገቢ ምንጭ ይጠቀማል፣

   ሸ/ የፌዴራሉና የክልሉ ሕገጋተ መንግሥታትና ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፣

www.abyssinialaw.com

ቀ/ የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የወረዳውን ባለሥልጣናት ለምያቋ ይጠራል፣የአስፈፃሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀጽ 88
## ስለምክር ቤቱ አመራርና አፈ ጉባኤ

1. የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እንዲኖረው ሆኖ ምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ተመርጦ በሚሰየም አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል።

2. አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራትና ጉባኤውን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል፣

3. ሌሎች የአፈ ጉባኤው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈ ጉባኤ አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገጉት እንደየአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 89
## የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ

ምክትል አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤውና ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ፣

1. በአፈ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አፈ ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 90
## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየስስት ወሩ ይሰበሰባል፣

2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል።

3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 91
### ስለወረዳ አስዳደር ምክር ቤት

1. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ ሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለወረዳው ምክር ቤት ነው።
2. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና አላማ አስፈፃሚ የሴክተር ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ሲሆን በብሄረሰብ አስተዳደሮች ውስጥ የሚገኙትን ሳይጨምር ከወረዳ ምክር ቤት በተጨማሪ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 92
### ስለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ/ የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እቅዶችና ፕሮግራሞች በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

   ለ/ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ያስተባብራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣

   ሐ/ በሕግ መሠረት የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ገቢዎችን ይሰበስባል፤ ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳው ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፣

   መ/ የወረዳውን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

   ሠ/ የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣ የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፣ሥራቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

   ረ/ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል። ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

   ሰ/ ሕዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያነሳሳል፣ የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል፣

   ሸ/ በወረዳው ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ቅርሳ ቅርስ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል።

   ቀ/ በወረዳው ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

2. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 93
### ስለ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

www.abyssinialaw.com

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ በወረዳ ምክር ቤት ምርጫ አሸናፊ በሆነውና በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት /ቶች/ከምክር ቤቱ አካላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 94
### የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የወረዳው አስተዳደር ሥራ መሪ፣ ያስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሣቢና አስተዳዳሪ ነው።
2. ዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆኖ፣

ሀ/ የወረዳውን አስተዳደር ይወክላል፣

ለ/ የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ይመራል፣

ሐ/ የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

መ/ ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳው ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል። ምክትል አስተዳዳሪው የምክር ቤት አባል መሆን አለበት፣

ሠ/ የወረዳ አስተዳደሩን ልዩ ልዩ ተቋማትና በሥሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ረ/ የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣የኢኮኖሚ ያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

ሰ/ የወረዳው ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ይቆጣጠራል፣

ሸ/ ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት፣ለወረዳው ምክር ቤትና ለበላዩ የአስተዳደር አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፣

ቀ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የወረዳውን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፣

በ/ በወረዳው ምክር ቤትና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 95

### የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በዋና አስተዳዳሪውና በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
3. ምክትል አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው።

## አንቀጽ 96

### የዋና አስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፣ ጽህፈት ቤቱ በዋና አስተዳዳሪው ተመርጦ በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል ።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል።
3. በዚህ ህገ መንግሥት ለርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደአግባብነቱ ለወረዳ ዋና አስተዳዳር ጽሕፈት ቤት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ምዕራፍ አሥር

### ስለቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 97

### አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግሥታዊ የአስተዳደር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ለታቀፈበት የከተማና ወይም የወረዳ አስተዳደር ነው።
2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል።

   ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት ፣

   ለ/ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤትና

   ሐ/ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ።

## አንቀጽ 98

### ስለቀበሌ ምክር ቤት

የቀበሌ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል።

የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ፣ተጠሪነታቸውም ለመረጣቸው ሕዝብ ነው።

የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤት ይሆናል፣

## አንቀጽ 99

### የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የወረዳው ምክር ቤትና የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጧቸው አቅዶችና መመሪያዎች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ የቀበሌን የሥራ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

2. የበላዩ የሆኑት የአስተዳደር አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መምሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ የአካባቢ ማህበራዊ ጉዳይ መመሪያዎችን አውጥቶ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የቀበሌውን አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና አስተዳዳሪ በምርጫ ይሰይማል፣ የቀበሌውን የአስተዳደር ምክር ቤት ያደራጃል፣

4. የነዋሪውን ሕዝብ ትችትና አስተያየት መሰረት በማድረግ በቀበሌው አስተዳዳሪ ተመርጠው የሚቀርቡለትን የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ይሾማል፣

5. የበላዩ በሆኑ የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ልማትና አስተዳደራዊ አቅዶችና ፕሮግራሞችን ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ ገሥራ ላይ የሚውሉበትን ዝርዝር የሥራ አፈጻፀም መርሃ ግብር ያወጣል፣ አፈጻፀሙንም ይከታተላል፣

6. ለሚመለከተው ቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ አቅዶችን ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም በቅርበት ይከታተላል፣

7. የቀበሌውን ነዋሪ ሕዝብ ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ሥራ በቅርበት ይከታተላል፣

8. የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት መጠበቁንና ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣

9. የቀበሌውን አስተዳዳሪና ምክትል አስተዳዳሪ ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈጻሚውን አካል አሠራር ይመረምራል፣

10. የቀበሌውን የአስተዳደር ምክር ቤትና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች የሥራ ክፍፍልና ምደባ ይወስናል።

## አንቀጽ 100

www.abyssinialaw.com

ስለቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት የሚኖረው ሆኖ ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ አፈ ጉባኤ እና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል፣

2. አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤት ሆኖ ምክር ቤቱን በየወቅቱ ይሰበስባል፣ ይመራል፣ አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባኤዎች መያዛቸውንና ሠነዶች መጠበቃቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

3. ምክትል አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤውና ለቀበሌው ምክር ቤት ሆኖ፣
   ሀ/ በአፈ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
   ለ/ አፈ ጉባኤው በማይገኝበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ -እርሱን ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 101

### የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌው ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሄዳል።

2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል።

3. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

4. የቀበሌው ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይደረግበት ወቅት አፈ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የቀበሌው አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 102

### ስለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት

www.abyssinialaw.com

1. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌው አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌው ምክር ቤት አማካኝነት በተጨማሪ ተመርጠው የሚሰየሙ ሆነው በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጭ የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞች በአባልነት የሚገኙበትና የበላዩ በሆኑት የአስተዳደር አካላት ለሚወጡ ሕጎች፣ደንቦችና መመሪያች የበታች አስፈፃሚ አካል ነው።

2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪ፣ ለመረጠው የቀበሌ ምክር ቤትና እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት ከተማ አስተዳደርና ወይም ለወረዳው አስተዳደር ይሆናል።

3. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ።

4. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በጋራ ሥልጣናቸው ለሚያሳልፉት ውሳኔና ለሚፈፅሙት ተግባር የጋራ የሆነ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 103

### የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ/ የቀበሌው ምክር ቤት የሚነድፋቸውን የልማት እቅዶችና ፕሮግራሞች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ ያውላል፣ የራሱን ዝርዝር የልማት እቅዶች ይነድፋል፣ ለቀበሌው ምክር ቤት አያቀረበ ያስፀድቃል፣

ለ/ በቀበሌው ውስጥ የሚካሄዱ የማህበራዊ አገልግሎት እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ/ የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ሕዝቡን ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ያስተባብራል፣

መ/ የቀበሌው ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣

ሠ/ በአካባቢው ለሚገኙት ቅርሳ ቅርሶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፣በጥቅም ላይ ስለሚውሉበት መንገድም የበላዩ ለሆኑት አካላት ያሳውቃል፣

ረ/ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፣ በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

www.abyssinialaw.com

2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ዝርዝር የሥራ አቅዶችን የሚነድፈውና አፈፃፀማቸውን የሚከታተለውም ሆነ የሚገመግመው እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል።

## አንቀጽ 104

### ስለቀበሌው አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ በቀበሌ ምክር ቤት ምርጫ አሸናፊ በሆነውና በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት/ቶች/ አቅራቢነት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል፣

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 105

### የቀበሌ አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደ ሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር ሆኖ የቀበሌው ዋና፣ የአስተዳደሩ ሥራ መሪና የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ/ የቀበሌውን የአስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ይመራል፣

ለ/ የበላዩ በሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚያወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አቅዶች ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ/ ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣

መ/ የነዋሪውን ሕዝብ አስተያየት መሠረት አድርጎ በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት አማካኝነት እንዲጣራ ካደረገ በኋላ እጩ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ዝርዝር ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፣

ሠ/ ለቀበሌው ምክር ቤት፣ ለነዋሪው ሕዝብና እንደ አስፈላጊነቱ ቀበሌው ለታቀፈበት ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በየጊዜው የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፣

www.abyssinialaw.com

ረ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 104 (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳዳሪው የቀበሌውን ምክር ቤት መስራች ጉባኤ ይጠራል፣

ሰ/ በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት በቀበሌው ምክር ቤትና እንደሁኔታው በሚመለከተው ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 106

### የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ በቀበሌው አስተዳዳሪ ተመርጦ ሹመቱ በቀበሌው ምክር ቤት የሚፀድቅ ሆኖ ፣

1. በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት እና በአስተዳዳሪው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣
3. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው።

## አንቀጽ 107

### ስለቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት

1. የቀበሌ አስተዳደር የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤትና የቀበሌው ምክር ቤት የቀበሌውን አስተዳደር ጽህፈት ቤት በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ ።
3. የቀበሌው ጽህፈት ቤት ኃላፊ በበላይነት የሚመራው የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ነው ።

## አንቀጽ 108

### የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 99 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር በተደነገገው መሠረት ተመርጠው የሚሾሙ ይሆናሉ።

3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት የሥራ ዘመን የቀበሌው የሥራ ዘመን ይሆናል።

## ምዕራፍ አሥራአንድ

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 109

### ዓላማዎች

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋተ መንግሥታት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት።
2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "መንግሥት" ማለት "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት" ማለት ነው።

## አንቀጽ 110

### ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

2. የክልሉ መንግሥት የብሄረሰቦችና የሕዝቦችን ማንነት የማክበር፣ በዚህም ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት።

3. የአገሪቱን ፈጣን የልማት ራዕይ እውን ለማድረግ ከሙስና የፀዳ፣ ግልጽ፣ተጠያቂ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መልካም አስተዳደር እስከ ቀበሌ መመሥረት ይኖርበታል።

## አንቀጽ 111

### ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ባላቸው እውቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት።

2. የክልሉ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

3. የክልሉ መንግሥት በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ ብሄረሰቦች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።

4. የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው ሕዝብ እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

5. የክልሉ መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅም እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

www.abyssinialaw.com

6. የክልሉ የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ሕዝቡ እንዲሳተፍ ማድረግ አለበት። የሕዝቡን የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት።

7. የክልሉ መንግሥት የሕዝቡን ዕውቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ሕዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ አለበት። ስለሆነም ሕዝቡ ዕቅዶችና ፖሊሲዎችን በመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት።

8. የክልሉ መንግሥት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

9. የክልሉ መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

10. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሥነ ምህዳር ማለትም ሰፊና ለም መሬት፣ በቂ ዝናብ በርካታ ትላልቅና ገባር ወንዞች መሠረት ያደረገ፣የክልሉን ተነፃፃር ብልጫዎች ላይ ያተኮረ፣ ፈጣን፣ የተሳሰረና በገበያ የሚመራ የልማት እንቅስቃሴ ያደርጋል። ለዚህም ሲባል የሕዝቡ የባለሀብቶችንና የመንግሥት የልማት ኃይሎች በቅንጅት ይመራል፣ የካፒታልና የጉልበት ዝውውር ያሳልጣል። ከአገሪቱ የገበያ ማዕከላት መሠረተ ልማት ለመዘርጋት ከፌራል መንግሥት ጋር ሙሉ ትብብር ያደርጋል።

## አንቀጽ 112

### ማህበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውኃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና ማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

2. ትምህርት ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል።

## አንቀጽ 113

### ባህል ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም ዲሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነው።

3. የክልሉ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ ጥበብን፣ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።

4. የክልሉ መንግሥት ወጣቱን ትውልድ የመን[illegible] www.abyssinialaw.com [illegible]ር ኃላፊነት የሚሸከም፣ ሀገሩን የሚወድና ለወገኑ የሚቆረቆር ብቁና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ያለሰለሰ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 114

### የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት።
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።
3. የሕዝብንና የአካባቢ ደህንነትን የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሀሳቡን እንዲገልፅ መደረግ አለበት።
4. የክልሉ መንግሥትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 115

### የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 1 /ለ/ና በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 2 (2.17) በተደነገገው መሠረት ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 59/ ንዑስ አንቀጽ 9 ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ያስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በሥራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አፈ ጉባኤው የክልሉን ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማስፀደቅ አለበት። ድንጋጌው በምክር ቤቱ ከግማሽ በላይ ድምፅ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል።

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ በሥራ ላይ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል።

4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና የክልሉ ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አማካኝነት የሚያወጧቸው ደንቦችና የሚወስዷቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16፣ አንቀጽ 17፣ አንቀጽ

www.abyssinialaw.com

19/1/ እና /2/፣ አንቀጽ 22/1/፣ አንቀጽ 25/1/፣ አንቀጽ 26፣ አንቀጽ 28/1/ እና አንቀጽ 39 ድንጋጌዎች ሥር የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

## አንቀጽ 116

### የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. በክልሉ ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።

2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

ሀ/ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሰሩ ግለሰቦች ቢኖሩ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለፅ፣

ለ/ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብዓዊ አለመሆናቸውን መከታተልና መቆጣጠር፣

ሐ/ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢ- ሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት ርዕሰ መስተዳድሩ ወይም መስተዳድር ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሃሳብ መስጠት፣

መ/ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃዎች ኢሰብዓዊ ድርጊት የፈፀሙ ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ሠ/ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው አፈፃፀም እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ።

3. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተልዕኮውን እንዳጠናቀቀ የሚፈርስ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 117
### የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ። ተጠሪነታቸውም ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል።

2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግሥት ተቋማትና የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ምክር ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ ውስጥ እንዲሠሩ ለተወሰኑት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል።
4. የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 118
### የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ስለማመንጨት

የዚህ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ፣

ሀ/ በክልሉ ምክር ቤት አባላት አንድ ሶስተኛ ጥያቄ ወይም፣

ለ/ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ያብላጫ ድምፅ ውሳኔ ወይም፣

ሐ/ በብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቶች አንድ ሶስተኛ ድምፅ ወይም፣

መ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዎቹ ጥያቄ ወይም፣

ሠ/በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የቀበሌ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛው ጥያቄ ለውይይትና ለውሳኔ የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ጉዳይ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል።

## አንቀጽ 119
### ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል

1. በዚህ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ምዕራፍ ሶስት የተዘረዘሩት መብቶችና ነፃነቶች ሊሻሻሉ የሚችሉት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለት እና ምዕራፍ ሶስት ሲሻሻሉ ብቻ ነው። ስለሆነም የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሻሻል በሚደረግበት ወቅት የዚህ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለት እና ምዕራፍ ሶስት ሊሻሻሉ የሚችሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ‹ሀ› እና ‹ለ› መሠረት ይሆናል፣

   ሀ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምፅ ሲያፀድቁትና፣

   ለ/ የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነው።

www.abyssinialaw.com

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተሉት አኳኋን ብቻ ይሆናል፣

ሀ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት የወረዳ ምክር ቤቶች በ ሁለት ሶስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁትና፣

ለ/ የክልሉ ምክር ቤት አባላት በአብላጫ ድምፅ ሲያፀድቁት ነው።

## አንቀጽ 120

### ነባር ህጎች ስለመሥራታቸው

በክልሉ ውስጥ እስካሁን ድረስ ፀንተው የሚሠራባቸው ነባር ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተሻሽሎ ከወጣው ከዚህ ህግ መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## አንቀጽ 121

### የመጨረሻ ህጋዊ ዕውቅና ስላለው ቅጅ

የዚህ ህገ መንግሥት የአማርኛ ቅጅ የመጨረሻው ህጋዊ ዕውቅና ያለው ሠነድ ነው።